ቀስተደመና ሬድዮ
ትችት 03.01.03

# ዘመናዊ አፋኝ፣ ያረጀ ያፈጀ አፋኝ

ከአመት በፊት መስከረም አንድ ቀን 1994 ኢ.ም. በኒውዮርክና በዋሽንግተን ከተሞች ሽብርተኞች አደጋ ጥለው ብዙ ጥፋት ካደረሱ ወዲህ የአሜሪካን መንግስት የውጭ ፖሊሲ ዋና አላማ በአለም አቀፍ ደረጃ ሽብርን ለማጥፋት የሚል አላማ ነው። ከምንም ከምንም ሌላ ነገር በላይ የዚህ አላማ መሳካት ላይ አተኩራለሁ የሚለው የፕሬዜዳንት ጆርጅ ቡሽ ፖለቲካ እንደዚሁ በአለም ደረጃ አንዳንድ ከባድ ጥያቄዎችን አስነስቱዋል። ከነዚህ ውስጥ አንዱና ብዙ እያወዛገበ ያለው ጥያቄ አሜሪካ ተገቢ የሆነውን ጸረ ሽብር ትግል ስታካሂድ ከማን ከማን ጋር እየተባበረች መሆን አለበት? ለዚህ ትግል አጋጅና ተባባሪ ስትመርጥ የገዛ ህዝቦቻቸው እንደአፋኝና እንደ ሽብርተኛ ከሚቆጥሩዋቸው ጸረ ህዝብ መንግስታት ጋር መተባበር አለባት ወይ? ይህ ትብብር ለራሱ ለጸረ ሽብሩ ትግልም ሆነ እነዚህ መንግስታት አፍነው ለሚገዙዋቸው ህዝቦች ሰላምና ደህንነት እንቅፋት አይሆንም ወይ? የሚሉ ጥያቄዎች ይቀርባሉ።

በአለም ደረጃ ስለ ሰብአዊ መብትም ሆነ ለህዝቦች ነጻነት የሚቆረቆሩ ሃይሎች ሁሉ ከአንድ አመት ጀምረው በዚህ ጉዳይ ብዙ ተችተዋል። ባጭሩ የሚሉትም ነገር ግልጽ ነው። ገና ለገና ሽብርተኞችን እዋጋለሁ በሚል አላማ አሜሪካ ልተባበር ከአለ መንግስት ጋር ሁሉ መተባበር የለባትም። ለጸረ ሽብሩ ትግል ሲባል ከጸረ ህዝብ መንግስታት ጋር መተባበር የህዝቦችን የመከራ ዘመን ያራዝማል። ዞሮ ዞሮ ደግሞ ህዝቦች ጭቆና ሲበዛባቸው ማመጻቸው ስለማይቀር ይህ ትብብር በህዝብ የተጠሉ መንግስታት ስር የሚኖሩ ህዝቦችን ቁጣ ቀስቅሶ አለመረጋጋት ስለሚፈጥር ለሽብርተኞች የተመቻቸ ሁኔታ ይፈጥራል የሚሉ ክርክሮች በተደጋጋሚ ቀርበዋል።

ይህንን ጉዳይ በማስመልከት ሂውማን ራይትስ ዎች የተባለው ዋና ጽህፈት ቤቱ ኒውዮርክ የሆነው የሰብአዊ መብት ተሙዋጋች ድርጅት ከአስር ቀን በፊት ለፕሬዜዳንት ጆርጅ ቡሽ አንድ ደብዳቤ ጽፎ ይፋ አድርጉዋል። ደብዳቤው የተጻፈው ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ድርጅቱ በሚያራምደው አቋዋም መንፈስ ነው። ለጸረ ሽብርተኞች ትግል መሳካት ሲባል ከአፋኝ መንግስታት ጋር መተባበር አደገኛ አካሄድ ነው የሚል መሰረታዊ ይዘት አለው። ግን የደብዳቤው ዋና አላማ ከአጠቃላይ አባባል አልፎ አሜሪካ በተለይ ከኢሳያስ አፈወርቂ ኤርትራ ጋር ያሰበችውን ትብብር የሚመለከትና ጆርጅ ቡሽ ከእንደዚህ አይነቱ አጉልና አደገኛ ሽርክና እንዲቆጠቡ የሚጠይቅ ደብዳቤ ነው።

ነገሩ ምንም አዲስ ነገር የለውም። ደብዳቤው በመጀመሪያ ባለፈው ወር የአሜሪካን የመከላከያ ሚኒስትር በአፍሪካ ቀንድ አገሮች ያደረጉትን የስራ ጉብኝት አውስቶ በዚህ ወቅት በአስመራ ባደረጉት ቆይታ ኢሳያስ አፈወርቂ ጸረ ሽብር ከተባለው ትግል ለመደባለቅና በግርግር የራሳቸውን የአፋኝነት ዝና ለማረሳሳት የአሰብን ወደብ ላዋጣ ብለው ያቀረቡትን ማመልከቻ የሚመለከት ነው። ድርጅቱ የመከላከያ ሚኒስትሩ ለዚህ የኢሳያስ ጥያቄ ተጨባጭ የሆነ መልስ አለመስጠታቸውንና ነገሩ አሁንም በእንጥልጥል መሆኑን ከጠቆመ በሁዋላ አሜሪካ ይህንን ጥያቄ እንዳታስተናግድ ይማጸናል። የሚያቀርባቸውም ክርክሮች ያው የተለመዱት ክርክሮች ናቸው። በአንድ በኩል ይህንን የኢሳያስን ጥያቄ መቀበል በኤርትራ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ እንዲሻሻል የሚደረገውን ትግል ያደናቅፋል። ሁለተኛ ደግሞ እንዲህ አይነቱ ትብብር ለራሱ ለጸረ ሽብሩ ትግል ጎጂ ነው የሚሉ ክርክሮች ናቸው።

ከዚህ መንደርደሪያ በመነሳት ሂውማን ራይትስ ዎች መላው አለም ያወቃቸውንና ፕሬዜዳንት ጆርጅ ቡሽም ቢሆኑ የማይስቱዋቸውን መጠን የለሽ ሰብአዊ መብት ረገጣዎችን ይዘረዝራል። ከአመት በፊት ታስረው የት እንደደረሱ ስለማይታወቁት ሁለት የአሜሪካ ኤምባሲ ሰራተኞች የሆኑ ኤርትራውያን፤ ከአመት በፊት በቁጥጥር ስር ውለው እስካሁን ፍ

ርድ ስላልቀረቡት የቀድሞ የሻብያ ባለስልጣናት፤ ጨርሰው ስለተዘጉ ነጻ ጋዜጦችና በቁጥ
ጥር ስር ስለዋሉ ጋዜጠኞች፤ ከሁለት ወር በፊት የኢሳያስ መንግስት ሲአይኤ ሊገለብጠኝ
አሲሮብኝ ነበር ብሎ ስላቀረበው ውንጀላ፤ ነጻ ምርጫ አለመካሄዱ፤ እንደ ጀሆባ ዊትነስስ
አይነት የሃይማኖት ስብስቦች ላይ ስለሚካሄደው ዘመቻ፤ በማውሳት አፋኙ የኢሳያስ መንግ
ስት ለጸረ ሽብሩ ትግል ተባባሪነት ብቁ አይደለም የሚለውን ክርክር አስፋፍቶ ለማቅረብ
ሞክሩዋል።

ሂውማን ራይትስ ዎች ከዚህ በመቀጠል በእንደዚህ አይነቱ ሁኔታ ውስጥ እያለን ከ
ኢሳያስ አፈወርቂ መንግስት ጋር ለመተባበር መሞከር ለዚህ መንግስት ሁኔታዎችን እንዲያ
ሻሽል ሳይሆን በያዘው አደገኛ ሂደት እንዲቀጥል ማድረግ ነው ብሎ ያስጠነቅቃል። በመ
ጨረሻም ራሳቸውን ጆርጅ ቡሽን በመጥቀስ

«ራስዎ በትክክል እንዳስቀመጡት የፖለቲካ አፈና ህዝቦችን መፈናፈኛ አሳጥቶ ወ
ደ አመጽ ስለሚመራቸው ለጸረ ሽብሩ ትግል አደገኛ ነው።» ይልና በነዚህና ሌላ ተዘርዝ
ረው በማያልቁ ምክንያቶች አሜሪካን በአፍሪካ ቀንድ ከእንደዚህ አይነቱ መንግስት ጋር ስ
ትተባበር መታየቱዋ ለራሱዋ ለአሜሪካ ዘላቂ ጥቅም የማያዋጣ ስለሆነ እየከፋ በመሄድ ላይ
ላለው አፈና ተገቢው መልስ ይበልጥ ትብብር ሳይሆን ሁኔታዎች እንዲሻሻሉ ይበልጥ ጫ
ና ማድረግ መሆን አለበት በማለት ሂውማን ራይትስ ዎች ደብዳቤውን ደምድሙዋል።

ይህንን ያየ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ራሱን አንዳንድ ጥያቄ መጠየቁ አይቀርም። ከነአቶ
መለስ ዜናዊ ጋር አሜሪካ የምታደርገው ትብብርስ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ እንዲያብብ የ
ሚያደርግ ትብብር ነው ወይ? ይህ ትብብር ዞሮ ዞሮ በሃገራችን አለመረጋጋት አይፈጥርም
ወይ? ይህስ ሽብርተኝነትን በአፍሪካ ቀንድ ለማስፋፋት አመቺ ሁኔታ አይፈጥርም ወይ? የ
ሚሉ ጥያቄዎች ይነሳሉ። የኛ መልስ እንዲህ አይነቱ ትብብር ለኢትዮጵያ ህዝብ ጎጂ እን
ጂ ጠቃሚ አይደለም የሚል ነው። ይህንን ብዙ ኢትዮጵያውያን ብለውታል። በቅርቡም
መለስ ዜናዊ አሜሪካ ተጠርተው ጆርጅ ቡሽ ጋር ሲቀርቡ በዋሽንግተን ዲሲ የወጣ ሰልፈ
ኛ በሁዋይት ሃውስ ቤተመንግስትና በአሜሪካን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፊት ለፊት ተሰብ
ስቦ ተቃውሞውን አሰምቱዋል።

እነሂውማን ራይትስ ወችም ሆኑ ሌሎች የሰብአዊ መብት ተሙዋጋች ድርጅቶች ለ
ጸረ ሽብሩ ትግል ሲባል አሜሪካን ከአፋኝ አገዛዞች ጋር መተባበር የለባትም የሚለውን ት
ክክለኛ አቋዋም ከያዙ አይቀር ይህንን አቋዋም ሁሉም ቦታ በሁሉም ሁኔታ ይዘው መጽና
ት አለባቸው። እኛም አገር በደርዘን ሽህ የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞች አሉ፤ መለስ ዜና
ዊም ቀንደኛ የነጻ ፕሬስ ጠላት ተብለው የተፈረጁ ናቸው፤ በኛም አገር በየጎዳናው ዜጎች
በጠራራ ጸሃይ ይረሸናሉ፤ ነጻ ምርጫም የተባለው ከዳር እስከዳር በተጭበረበረ አካሄድ ወ
ያኔ ዘጠና ስምንት ከመቶ የፓርላማ ወንበር አሸንፍኩ እያለ የሚመጻደቅበት ግርግር ብቻ
ነው።

ይህንን ካልን ዘንዳ ምንም አርኪ መልስ ለጊዜው ባናገኝለትም እነመለስ ዜናዊ ብቁ
ናችሁ ተብለው እነአቶ ኢሳያስ ግን ለጸረ ሽብሩ ትግል ተባባሪነት ብቁ አይደላችሁም የሚ
ባሉበት መስፈርት ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ይመስለናል። ሁለቱም ከ
ዚህ ትግል ተደባለቅን በማለት የአሜሪካንን ድጋፍ ለማግኘት ይሙዋሙዋታሉ። ኢሳያስ ይ
ህንን አላማቸውን ለማራመድ አልፈው ተርፈው አሰብን ውሰዱልኝ ተጠቀሙልኝ ለማለት
በስድስት መቶ ሽህ የአሜሪካን ዶላር አማላጅ ቢሮ ቀጥረዋል። አሜሪካኖች ግን ለኢትዮጵ
ያ ሲሆን አጥብቀው የማያነሱትን የሰብአዊ መብት ጥያቄ እየጠቆሙ ከኢሳያስ አሰብን ለ
መረከብ እያቅማሙ ናቸው። ይህ የሚሆነው አሰብን ባለመፈለጋቸው አይደለም። ተቃዋሚ
ተብየው ኤርትራዊም ቢሆን «አሰብን ከኢሳያስ አትቀበሉ። እኛም ብንሆን እንነፍጋችሁም
።» በማለት በይፋ ቃል ገብቶላቸዋል። እነመለስ ዜናዊም በበኩላቸው የአሰብን ጉዳይ ከ
ዚህ አካባቢውን ከሚያምስና ጠብ አጫሪ ከሻብያ አገዛዝ ይልቅ አፍቃሬ ወያኔ ከሚሆን
ሌላ የኤርትራ መንግስት ብትቀበሉ ይሻላል የሚል ቅስቀሳ ያካሂዳሉ። በመሃል ግትሩ ኢሳ
ያስ አልፈው ተርፈው የጎረቤት አልበቃ ብሎዋቸው ሲአይኤ ሊገለብጠኝ አስቦ ነበር ብለ
ው በይፋ መወንጀላቸው ሰውየውን ይበልጥ ችግር ላይ ጥሎዋቸዋል።

ኢሳያስ እየተወረደባቸው መለስ ቢረሱ የዚህ ምክንያት ቀላል ይመስለናል። መለስ አፈ ጮሌ የሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን አፋኝ ናቸው። ኢሳያስ ጊዜ ያለፈባቸው ያለፈው ክፍለ ዘመን ዲክታተር ናቸው። የኛው አፋኝ ገጂ ዋሽንግተን ጆርጅ ቡሽ ፊት ባደረጉት ንግግር ጸረ ሽብሩ ትግል የሚደረገው « ወደ ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን መሻገር ካቃታቸው ሁዋላ ቀር ሃይሎች ጋር ነው» ሲሉ የፕሬዜዳንቱን ልብ የነካ ንግግር አድርገው ነበር። እንደበታቸው ስለአለፈው ክፍለዘመን ሽብርተኞች ሲናገር ልባቸው ወደ ኢሳያስ ሄዶ ስላለፈው ክፍለ ዘመን አፋኝ አገዛዞች ያስብ እንደነበረ ግልጽ ነው። የነጆርጅ ቡሽን ልብ ይነካ እንደሆን እንጂ ለኛ ግን ምንም የሚለወጥ ነገር የለውም። ዘመናዊና ጮሌ አፋኝ በአንድ በኩል ያረጀ ያፈጀ ያለፈው ክፍለዘመን አፋኝ በሌላ በኩል። ለሃገራችን ሲባል ከአፈ ጮሌና ዘመናዊ ነኝ ባይ አፋኝ ግትርና ሁዋላ ቀር አፋኝ ቢያድለን ኖሮ ምናልባት እስካሁን ተገላግለን ነበር። ማን ያውቃል?